በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

## መምህር፦ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፦*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ነሐሴ ፲፩ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.**

# <u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ</u>

***<u>መግቢያ</u>***

- *በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለምናደርገው ጉዞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅና ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ እግዚአብሔር በሙላት በሕይወታችን መኖሩን የምንረዳበት ብቸኛው መንገድም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅና በማድረግ ነውና፡፡*
- *መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ የምንችልበትን ፎርሙላ (ስሌታዊ መንገዶች) ይሰጠን ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ዕቀድ በርግጠኝነት ልናውቅ የምንችልበትን አቅጣጫ ለይቶ ተንትኖ አያስነብበንም፤ ይሁን እንጂ በነገር ሁሉ ያሳየን ዘንድ በጌታችን በአምላካችን የመደገፋችንን አስፈላጊነት ግን በግልጽ አስቀምጦልናል፡፡*
- *ስለዚህ በኛ በኩል በሕይወታችን በማስተዋል ሁሉ የርሱን ፈቃድ በማስተዋል እንድንሻና በርሱም በኩል በጌታችን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ አመራር በግድ አንድንደገፍ ይገባናል፡፡*
- *በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ የምንችልበት ፎርሙላ (ስሌታዊ መንገዶች) ያለመገኘታቸው ምክንያቱ እግዚአብሔር ሊያስተምረን እንጂ ሊመራን አለመሻቱ ነው፡፡* ‹‹አስተምርሃለሁ በምትሄድበትም መንገድ እመራሃለሁ ዓይኖቼን በአንተ ላይ አጠናለሁ። ወደ አንተ እንዳይቀርቡ በልባብና በልጓም ጉንጫቸውን እንደሚለጉሙአቸው፥ ልብ እንደሌላቸው እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ።›› ***<u>መዝ 31(32)፡8-9፡፡</u>***
- *እግዚአብሔር ለእኛ ፈቃዱን የሚገልጥባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ እግዚአብሔርን ፈጽመን መርምረን ልንደርስበት እንደማንችለው ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገለጥባቸው መንገዶችን ሁሉ ዘርዝረን አንዘልቃቸውም፡፡ ይሁን እንጂ ፈቃዱን ለእኛ ከሚገልጣባቸው መንገዶች የሚበዙትን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡*

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

## 1. ከእግዚአብሔር ቃልና ከሕጉ ጋር መስማማት

- የእገዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅት የመጀመሪያው ደረጃ ከእግዚአብሔር ቃል (ከመጽሐፍ ቅዱስ)፣ ከቤተ ክርስቲያንና ከቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች ጋር መስማማት ነው፡፡
- ቤተ ክርስቲያንና መጽሀፍ ቅዱስ የሚሉንን ሁሉ መውደድ፣ ትክክል እንደሆነ መቀበልና ትምህርቱና ቃላቱም ተነጻጻሪና ተፎካካሪ የሌለው ፍጹም እውነት መቀበል አለብን፡፡ ‹‹ አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ፥ ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው። ›› ***መዝ 39 (40)፡8*** እንዳለ ልበ አምላክ ዳዊት፡፡
- የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅበት የማዕዘን ድንጋይ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ዘወትር መጽሐፍ ቅዱስን የምናነብና የምንጽናናበትም ከሆን አዲስ የአስተሳሰብና የአመለካከት በር በሕይወታችን ይከፈታል፡፡
- በአንድ ጉዳይ የእግዚአብሔርን ምሪት ስንፈልግም ስለዚህ ጉዳይ የእግዚአብሔር ቃል የሚነግረንን ማስታወስ የምንችልበት አጋጣሚ ይፈጠርልናል፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጥና የፍቅር ደብዳቤው መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ባይኖር የማዳኑን ነገር መረዳት ባልቻልን ነበር፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ እንደ አሠርቱ ትእዛዛት የእግዚአብሔርን የምግባር ሚዛን የሚነግረን መጽሐፍ ነው፡፡ ‹‹ ወደ ሕግና ወደ ምስክር ሂዱ! እንዲህም ያለውን ቃል ባይናገሩ ንጋት አይበራላቸውም። ›› ***ኢሳ 8፡20*** በማለት ሕግና ምስክር እንደ ቃሉ ባይናገሩ በውስጣቸው ብርሃን ባልተገኘ ነበር በማለት ብርሃን ያለበትን የእግዚአብሔርን ሕግ ምግባር እንድንይዝ አነሳስቶናል፡፡
- በምንወስንበት ጊዜ የሚጠቅመንን እውነት እንድናገኝ መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ምሪትን ይሰጠናል፡፡ ለዚሁ ነው ልበ አምላክ ዳዊት ‹‹ ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው።›› ***መዝ 118(119)፡105*** ያለው፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሚገለጥበት መዝገብ ነው፡፡

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

## 2. ለእግዚአብሔር ፈቃድ መሸነፍ

- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ በቅድሚያ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ምኞትና ፈቃደንነት እንዲኖረን ይገባል፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ሕይወታችንን ለመድኄዓለም አሳልፈን መስጠት አለብን፡፡ ሕይወታችንን ከሰጠነውም የፈቃዳት ውኅደት ይፈጠራል፤ የርሱ ፈቃድም የኛ ፈቃድ ይሆናል፡፡ ይህን አስመልክቶ ጌታችን በጌቴሴማኒ ታላቅ ምሳሌ ሰጥቶናል፡፡ ‹‹ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ። አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ።›› ***ማቴ 26፡39፡፡*** እንዳለ፡፡
- ለመፈጸም ዝግጁነትና ፈቃደኝነት ከሌለን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቃችን ጥቅም የለውም፡፡
- እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚገልጽልን ሕይወታችንን ወደርሱ ስንመልስና ይመራንም ዘንድ ሙሉ ለሙሉ ስንደገፍበት ነው፡፡ ራስን መስጠትም ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ጥብቅ ወዳጅነት መመሥረትን ይፈልጋል፡፡
- ስለዚህ ፈቃዱን ለማወቅ ፈቃዱን ለማድረግ ዝግጁነት ይኑረን፤ ይህም የሚደረገው ጥብቅ ወዳጅነት ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ስንመሠርት ነው፡፡
- ለፈቃድ በመታዘዝም ታላቁ ምሳሌያችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በእርሱ ፈቃድ በአባቱም ፈቃድ ሰውን ለማዳን ወደ ዓለም መጥቷልና፡፡ ‹‹ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና።›› ***ዮሐ 6፡38*** እንዳለ፡፡
- እኛ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ፈቃደኞች ከሆን እግዚአብሔርም ፈቃዱ ምን እንደሆነ ይገልጽልናል፡፡ ‹‹ ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል። ›› ***ዮሐ 7፡17፡፡***

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

## 2. ለእግዚአብሔር ፈቃድ መሸነፍ

- ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የራሳችንን ሕይወት ዕቅድ ማስተካከል እንደማያስፈልገን ‹‹ አሁንም። ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን በዚያም ዓመት እንኖራለን እንነግድማለን እናተርፍማለን የምትሉ እናንተ፥ ተመልከቱ፥ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና። ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋዋለት ናችሁና። በዚህ ፈንታ። ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል።›› ***ያዕ 4:13-15፡፡***
- ***በትንቢተ ኤርምያስ 29:11*** ለእኛ የሆነው የእግዚብሔር ፈቃድ ለራሳችን ካሰብነው ሐሳብ ከተከተልነው ፈቃዳችን ይልቅ የሚጠቅም እንደሆነ ‹‹ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም።›› በማለት አረጋግጦልናል፡፡
- በሌላ በኩል የእግዚአብሔርን ትተን የራሳችንን ሐሳብ ብቻ መከተላችን ፍጻሜው ሐዘን፣ ሞትና ጥፋት እንደሆነ ‹‹ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው።›› ***ምሳ 16:25*** በማለት ነግሮናል፡፡

## 3. እግዚአብሔር ወደ ፈቃዱ ይመራን ዘንድ ሳናቋርጥ መጸለይ

- ጸሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ቁልፍ ነገር ነው፡፡ ከጸሎት በቀር እግዚአብሔርን የምንገናኝበት መንገድ የለንም፡፡ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገረው ንግግር ነው፡፡ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስንም ቀርበን የምናውቅበት ምርኩዝ ጸሎት ነው፡፡
- እግዚአብሔር አዋቂ ስለሆነ ምን እንደምንፈልግ ያውቃል፤ ይሁን እንጂ ስለተወሰነ ጉዳያችን ግን ይረዳን ዘንድ እንድንጠይቀው ይሻል፡- ምክንያቱም ነገር ሁሉ በርሱ ፈቃድ እንደምትደረግ አውቀን ዘወትር የመጠየቅን ሥርዓት እንድንማር ስለሚሻ ነው፡፡ ‹‹ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።›› ***ዮሐ 14:14*** በማለት ፈቃዱ ለሕይወታችን እንድትደረግ የምንሻት ከሆነ ዘወትር እንደምትደረግልን ያረጋገጠልን ይህንኑ ነው፡፡

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

## 3. እግዚአብሔር ወደ ፈቃዱ ይመራን ዘንድ ሳናቋርጥ መጸለይ

- **ወደ ፈቃዱ ይመራን ዘንድ ሽተንም ሆነ ስለማንኛውም ነገር ስንጸልይ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ እንደጻፈልን በእምነት መሆን ይኖርበታል፡፡** ‹‹ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል። ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና።
- ›› ***ያዕ 1፡5-6፡***
- **ስለሌሎች መጸለይም የእግዚአብሔር ፈቃድ ፈጥና ለእኛም ሆነ ለምንጸልይላቸው እንድትደረግ ያደርጋታል፡፡** ‹‹ እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች። ›› ***ያዕ 5፡16፡፡***
- **ማንኛውንም ነገር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በጸሎት ብንጠይቅ እንደሚሰማን ድፍረት ይኑረን፡፡** ‹‹ በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል። ›› ***ቀዳ ዮሐ 5፡14፡፡***

## 4. በቅድሚያ በአጠገባችን ያለውን መፈጸም

- **የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅበት ትልቁ እድል በዙሪያችን ያሉትን ወደ መንገዳችን የገቡትን በመመርመር የገጠሙንን እድሎችና ምቹ አጋጣሚዎች መጠቀም መሆኑ ይበልጥ ተቀባይነት አለው፡፡**
- **ለምሳሌ ሌላ ቦታ ሄደን ረጅም መንገድ ነድተን ለማገልገል ከመወሰን ይልቅ በራሳችን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማገልገል፡፡ ስለዚህም በዙሪያችን ባልንጀርነትና መቀራረብ እንዲኖር ሁኔታዎችን ማመቻቸትና በአጋጣሚዎቹም በምናገኛቸው ዕድሎች መጠቀም አለብን፡፡ ስለዚህ በአቅራቢያችን ወዳሉ ዕድሎች ማተኮር አለብን፡፡**
- **እግዚአብሔር በተወሰነ ቦታ የሚያኖረን ፈቃዱእንድንፈጽምለት ሲል በምክንያት ነው፤ የእግዚአብሔርም ፈቃድ ዘወትር በቅርብ ናት፡፡**

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

## 4. በቅድሚያ በአጠገባችን ያለውን መፈጸም

- **ሁልጊዜ ነገሮችን ተራ በተራ ማድረግ እንጂ በርካታ ነገሮችን በአንዴ ለማድረግ መጣደፍ ወይም ከሚገባው በላይ ስለወደፊቱ መመልከት የለብንም፤ እግዚአብሔር የሚገልጥልን ለጊዜው አስፈላጊ የሆነውን ፈቃዱን ብቻ ነውና።**
- **እኛም ትኩረት ማድረግ ያለብን ወደ ተገለጸችልን ፈቃዱ እንጂ ስለወደፊቱ በማይገባ ልክ መወጠር የለብንም። ለምሳሌ ስለ መኖሪያ ቤታችን፣ ልጆቻችን፣ ጓደኞቻችን፣ ሥራችን፣ ትዳር፣ አገልግሎት፣ ወዘተ እግዚአብሔር በአጠገባችን ያደረገውን እንመልከት።**
- **ጌታችን የሚነግረን ብዙ ቢኖርም** ‹‹የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም።›› ***ዮሐ 16:12*** **እንዳለን አሁን የምናውቀውንና ትክክል የሆነውን እናድርግ፤ ከዚያም ቀጥለን ምን ማድረግ እንዳለብን ያመለክተናል።**
- ***በምሳሌ 3:6*** ‹‹በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፥ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል።››፣ ***በሉቃ 16:10*** ‹‹ከሁሉ በሚያንስ የታመነ በብዙ ደግሞ የታመነ ነው፥ ከሁሉ በሚያንስም የሚያምፅ በብዙ ደግሞ ዓመፀኛ ነው።›› **በማለት በጢቂቱ ስንታመን ብዙውን እንደሚገልጽልን፣** ***በኤር 12:5*** ‹‹ከእግረኞች ጋር በሮጥህ ጊዜ እነርሱ ቢያደክሙህ፥ ከፈረሶች ጋር መታገል እንዴት ትችላለህ? በሰላምም ምድር ታምነህ ብትቀመጥ፥ በዮርዳኖስ ትዕቢት እንዴት ታደርጋለህ?›› **በማለትም በጥቂቱ በእግዚአብሔር ካልታመን ታላቁ ፈተና ሲመጣ እንዴት ልንታዘዘው እንችላለን በማለት በአጠገባችንና በቅርባችን ባለው እንድንታመን ነገረውናል።**

## 5. ዘወትር ለእግዚአብሔር ታላቁን ክብር የሚያስገኘውን ምርጫ ምረጡ

- ***ቀዳ ቆሮ 10:31-32*** ‹‹እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት። እኔ ደግሞ ብዙዎቹ ይድኑ ዘንድ ለጥቅማቸው እንጂ የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ በሁሉ ነገር ሰውን ሁሉ ደስ እንደማሰኝ፥ ለአይሁድም ለግሪክም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማሰናከያ አትሁኑ።››፣ ***ቀዳ ጴጥ 4:11*** ‹‹ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን።›› **እንዳሉን።**

# <u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ</u>

## 5. <u>ዘወትር ለእግዚአብሔር ታላቁን ክብር የሚያስገኘውን ምርጫ ምረጡ</u>

- **በዘመኑ ፍጻሜ የበዛው ዓለም ክብርን ለእግዚአብሔር እንደማይሰጥ በማወቅ የተሰጠን ማስጠንቀቂያም** ‹‹ በታላቅ ድምፅም። የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት፤ ሰማይንና ምድርንም ባሕርንም የውኃንም ምንጮች ለሠራው ስገዱለት አለ። ›› ***<u>ራእ 14፡7</u>***
- **በዘወትር ኑሮአችን የምንወስነውም ውሳኔ ከማን ወገን እንደሆን ምስክርነትን የሚሰጥ ነው፡፡** ‹‹ እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ እርስ በርሳችን አንፈራረድ፤ ይልቁን ግን ለወንድም እንቅፋትን ወይም ማሰናከያን ማንም እንዳያኖርበት ይህን ቍረጡ።›› ***<u>ሮሜ 14፡13</u>***፣ ‹‹ በእኔም ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ ትልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይሻለው ነበር። ›› ***<u>ማር 9፡42፡፡</u>***

ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org